אגודת יהודי
אתיופיה בישראל

קו לעובד
Worker's Hotline
عنوان العامل

# ለእስራኤል ሠራተኞች የመብት ማሳወቂያ ( ሰኔ 2023)

**ዝቅተኛ ክፍያ**

ለሙሉ ጊዜ የሥራ ዝቅተኛ ክፍያ (በወር 182 ሰዓታት)፣ **5,571.75** ሼቁል፣ ለሳዓት፣ **30.61** ሼቁል፣ የሙሉ ጊዜ ሥራ 6 ቀናት በሳምንት ለሚሰሩ **222.87** ሼቁል፣ ሙሉ ጊዜ ሥራ 5 ቀናት በሳምንት ለሚሰሩ **257.16** ሼቁል (በማንኛውም ሁኔታ በሰዓት ከ 29.12 በታች አይሆንም)፡፡

**የሚከፈለበት ቀን**

የተወሰነ የሥራ ደመወዝን ከሚቀጥለው ወር 9 ኛው ቀን ባላለፈ አሠሪው መክፈል አለበት። ሠራተኞች እና አሠሪዎች የወር ደመወዝ በቀን መቁጠሪያ ወር ባልሆነ የአንድ ወር ክፍያዎች እንደሚከፈል መስማማት ይችላሉ፡፡ በእነዚህ ሁኔታዎች አሠሪው "የተስማሙበት ወር" ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ እስከ 9 ቀናት ድረስ ወርሃዊ ደመወዝን የመክፈል ግዴታ አለበት (ለምሳሌ- አንድ አሠሪ ከኦጉስት 24 እስከ ሰፐተምበር 23 - በኦክቶበር 1 ይከፍላል)፡፡

**ተጨማሪ ሰዓቶች**

ተጨማሪ የሥራ ሰዓት ክፍያ፣ 6 ቀናት በሳምንት ለሚሠራ፣ በቀን ከ 8 ሰዓታት ሥራ በኋላ ተጨማሪ ሰዓት ክፍያ እና 5 ቀናት በሳምንት ለሚሰራ፣ 8 ሰዓት ከ 24 ደቂቃዎች በኋላ ነው፡፡ እንዲሁም አንድ ሠራተኛ በሳምንት ከ 42 መደበኛ ሰዓቶች በላይ የሚሠራ ከሆነ ከመጀመሪያዎቹ 42 ሰዓቶች ካለፈ ትርፍ ሰዓት ነው (ለምሳሌ-በሳምንት 6 ቀናት የሠራ ሠራተኛ - 5 ቀናት 8 ሰዓት እና አርብ 5 ሰዓት - 42 መደበኛ ሰዓታት እና 3 ተጨማሪ ሰዓት ሠርቷል)፡፡ የተጨማሪ ሰዓት የሚታሰበው በተወሰነ የሥራ ቀን ወይም በተወሰነ የሥራ ሳምንት ውስጥ ባለው የሰዓት ብዛት ነው (እና በሌሎች ቀናት ወይም ከሳምንታት የሚጋባ ሰዓት አይደለም)። **ክፍያ፡** በዝቅተኛ ክፍያ መሰረት ለመጀመሪያዎቹ ሁለት ሰዓታት - 125% (በሰዓት **38.26** ሼቁል)፣ ከመጀመሪያዎቹ ሁለት ሰዓቶች በላይ በየሰዓቱ - 150% (በሰዓት **45.92** ይከፈላል)፡፡

**የሥራ ሰዓቶችን ምዝገባ**

የሥራ ሰዓቶችን (የመጀመሪያ እና የማብቂያ ጊዜ) መዝግቦ መያዝ አስፈላጊ ነው፣ ምናልባት ከአሠሪው ጋር አለመግባባት ከተፈጠረ ማስረጃ እንዲሆን፡፡

**የመጓጓዣ ወጪዎች**

አሠሪው የሥራ የጉዞ ወጪን በቀን እስከ 22.60 ሼቁል ድረስ ተመላሽ ማድረግ አለበት፡፡

**ሳምንታዊው የእረፍት ቀን**

የ 36 ተከታታይ ሰዓታት የሰራተኛውን የሃይማኖቱን የእረፍት ቀን አካትቶ (ለአይሁድ፣ ቅዳሜ) መሠረት ሳምንታዊ የእረፍት ቀን፡፡ በእረፍት ቀን ከሠራ ከቀኑ ደመወዝ 150% እና ከአማራጭ የእረፍት ቀን በተጨማሪ ነው፡፡

**ዓመታዊ ዕረፍት**

ሰንበታትን አልባ 14 ቀናት በዓመት፣ ስድስት ቀን በሳምንት ለሚሠሩ፣ 12 ቀናት በዓመት ሰንበታትን አልባ 5 ቀናት ለሚሠሩ ለመጀመሪያዎቹ 5 ዓመታት፡፡ በስድስተኛው ዓመት የእረፍት ቀናት ቁጥር ይጨምራል፡፡

**የባዓላት ቀናት**

እያንዳንዱ ሠራተኛ በዓመት 9 የባዓላት ዕረፍት ቀን ተገቢው ሲሆን ለአይሁድ፡ 2 የብርሐን ሰርቀ ቀን፣ የአስተራይ ቀን፣ የባዓለ መጸለት የመጀመሪየው ቀን፣ ሲምኻት ቶራ፣የፋሲካ የመጀመሪየው እና የመጨረሻው ቀናት፣ ዮም ሃአጽመኡት እና የሰኔ ማእረር፡፡ ከ 3 ወር ሥራ በኋላ መደበኛ የሥራ ቀኑ በእረፍት ቀን የሚውል ሠራተኛ ባይሠራም በመደበኛ ደሞዙ እኩል የሆነ ክፍያ የማግኘት መብት አለው፡፡

በበዓሉ ቀን የሠራ ሠራተኛ ለመጀመሪያዎቹ 8 የሥራ ሰዓታት የ 150% ክፍያ፣ ለዘጠነኛው እና ለአሥረኛው የሥራ ሰዓት 175% ክፍያ እና ለ 11 ኛው ሰዓት 200% ክፍያ የማግኘት መብት አለው፡፡ ይህ ከእረፍት ክፍያ በተጨማሪ ነው (ማለትም-ለመጀመሪያዎቹ 8 ሰዓታት 250%፣ ለ 9 ኛ እና ለአሥረኛው ሰዓታት 275%፣ እና ከ 11 ኛው ሰዓት ጀምሮ 300% እሱ ያገኛል)፡፡

**የማመጣጠን ክፍያዎች (ሀብራአ)**

አንድ ዓመት ሥራውን ያጠናቀቀ ሠራተኛ፣ ለ 5 ቀናት የሀብራአ መብት ለቀን 378 ሼቁል አለው፡፡ በሁለተኛው እና በሦስተኛው ዓመት - 6 ቀናት፣ ከአራተኛ እስከ አሥረኛው - 7 ቀናት፣ ከ 11 እስከ 15 ዓመት የ 8 ቀናት ሀብራአ፣ 16 ዓመት- 20 9 ቀናት ሀብራአ፣ ከዚያ በኋላ 10 ሀብራአ ቀን በዓመት፡፡ በሰዓታዊ ሥራ ተቀጥሮ የሚሠራ ሠራተኛ እንደ ሥራው ጊዜ የሀብራአ መብት አለው፡፡

**የሥራውን ስፋት አሰላል**

የሳምንት የሥራ ሰዓቶችን ብዛት በ 42 ሰዓታት ማካፈል፡፡

אגודת יהודי
אתיופיה בישראל

קו לעובד
Worker's Hotline
عنوان العامل

**ዕረፍቶች**

አቅም ጠያቂ የቀን ሥራ ውስጥ ተቀጥሮ የሚሠራ ሠራተኛ ከ 6 ሰዓታት ሥራ በኋላ የ 3/4 ሰዓት ዕረፍት የማግኘት መብት አለው፣ ቢያንስ 1/2 ሰዓት በቀጣይ ጊዜ መሆን አለበት (አቅም ጠያቂ የቀን ሥራ ካልሆነ- ከ 8 ሰዓት ሥራ በኋላ 3/4 ሰዓት)፡፡ በእረፍት ምክኛት የክፍያ ቅነሳ፡ - ሠራተኛው ከሥራ ቦታው እንዲወጣ ከተፈቀደለት፣ አሠሪው ከሠራተኛው ደመወዝ የእረፍት ጊዜውን መቀነስ ይችላል።

**የህመም ቀናት**

ታሞ ከሥራ ያልተገኘ ሠራተኛ - በሕክምና የምስክር ወረቀት መሰረት አሠሪው ደመወዝ መክፈል አለበት፡፡ ለመጀመሪየው ቀን አይከፈልም፡፡ ሁለተኛውና ሦስተኛው፣ ከዕለታዊ ደመወዝ 50%፡፡ ከአራተኛው ቀን ጀምሮ ከቀን ክፍያ 100%፡፡

**የሥራ መሰናበቻ ካሳ ክፍያ**

አንድ ዓመት ሥራ ከጨረሰ በኋላ ሠራተኛው ካሳ የማግኘት መብት አለው፣ ይህም ከሥራ ከተባረረ ወይም በልዩ ሁኔታ ምክንያት ሥራው ከተቋረጠ፣ ለምሳሌ፡ የሥራ ሁኔታ በመቀየሩ፣ በሰራተኛው የጤና ጉዳይ፣ ልጅን ለማሳደግ ሲባል ሥራ ካቋረጠ (ህፃኑ 9 ወር እስኪሞላው ድረስ) ወይም ደመወዝ እና ማህበራዊ መብቶቹ ካልተሟሉ፡፡

**ከስራ የመባረር / የሥራ መልቀቂያ አስቀድሞ ማስታወቂያ**

ሰራተኛው እና አሠሪው ከመልቀቂያ/ ከመባረር በፊት የቅድሚያ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት አለባቸው፡ ለመጀመሪያ ዓመት - አንድ ቀን ለወር፣ በሁለተኛው ዓመት- 14 ቀናት ለወር + ግማሽ ቀን ለወር። በሦስተኛው ዓመት - 21 ቀናት ለወር + ግማሽ ቀን ለወር። ከ 3 ዓመት ሥራ በኋላ ወይም ከዚያ በላይ - አንድ ወር። <u>ክፍያ</u> - ቅድመ ማስታወቂያ አንዱ ወገን ለሌላው ወገን ያልሰጠ፣ ለሚመለከተው ወቅት በደመወዝ መጠን ካሳ መክፈል አለበት፡፡

**የጡረታ አበል**

በ 2008 የትዕዛዝ መስፋፋት መሠረት እያንዳንዱ ሰራተኛ በእስራኤል፣ ሥራ ከጀመረበት ከሰባተኛው ወር ጀምሮ ከአሠሪው የጡረታ አበል የማግኘት መብት አለው፣ እንዲሁም የጡረታ ፈንድ ካለው (ካለፈው 5 ወራት ውስጥ ለጡረታ ፈንድ ተቀራጭ ክፍያ ከኖረው) ከሌላ የሥራ ቦታ አሠሪው ወርሀዊ ክፍያ አርጎለት ከሆነ፣ ከ 3 ወር በኋላ የጡረታ ክፍያውን ሥራ ከጀመረበት ቀን ጀምሮ ደጎም አለበት፡፡

በ 2021 ለጡረታ ፈንድ የሚውሉት ክፍያ እነህ ናቸው፡ ከሠራተኛው 6% ለክፍያ ጥቅማጥቅም፣ ከአሠሪው ደግሞ 6.5% ለጥቅም እና ለሌላ 6% ደግሞ ለካሳ ክፍያ የሚሆኑ ናቸው፡፡ ለጡረታ ፈንድ መመደብ ያለባቸው የደመወዝ ክፍሎች፡ መደበኛ የሰዓት ደመወዝ (ቅዳሜ / በዓላት የሠራተኛው መደበኛ ሥራ ዕለታት ከሆነ፣ ከነዚህ ሰዓታት ጀምሮ ለጡረታ ፈንድ መመደብ አለበት ነገር ግን እንደ መደበኛ የሥራ ሰዓት ዋጋ እንጂ እንደ ቅዳሜ / ባዓላትል አይደለም)፣ የህመም እና የዕረፍትክፍያን ጨምሮ። አንድ ሠራተኛ በደመወዝ + ተጨማሪ/ ወለዶች መሠረት ተቀጥሮ የሚሠራ ከሆነ ከተጨማሪ/ወለዶች እንዲሁ ለጡረታ ፈንድ መመደብ አለባቸው፡፡

**ከዓመቱ ከፊል ሥራ**

የዓመት የዕረፍት ጊዜ እና የባዓላት ቀናት በክፍያለማግኘት በዓመቱ ከፊሉን ለሠሩ (አንፃራዊውን ድርሻን ይቀበላል)ሁሉ ነው፡፡ የህብራአ እና የሥራ ስንብት ክፍያ መብት፣ በዓመቱ ውስጥ በከፊል ለሠሩ (አንፃራዊው ክፍል) ይሰጣል፣ ሠራተኛው ለአሠሪው <u>ቢያንስ አንድ ዓመት ሥራውን</u> ያጠናቀቀ ከሆነ፡፡

**እርግዝና እና መውለድ**

በተቀጠረችበት የመጀመሪያ ዓመት ውስጥ የምትወልድ ሠራተኛ የ 16 ሳምንታት ባለ ደመወዝ የወሊድ ዕረፍት መብት አላት፡፡ ከአንድ ዓመት በላይ የሠራች ሠራተኛ - ለ 26 ሳምንታት የወሊድ ዕረፍት መብት ሲገባት፣ ከዚህ ውስጥ 15 ሳምንቶች በክፍያ፣ ቀሪው ደግሞ ይለ ክፍያ፡፡ ረዘም ላለ ጊዜ ከመወለድ በፊት የሰራች ሰራተኛ እስከ አንድ አመት ገደብ ድረስ ከቅጥር ጊዜዋ ሩብ የማግኘት መብት አላት፡፡

በሥራ ቦታ ከ 6 ወር በላይ ተቀጥራ የሰራች ነፍሰ ጡር ሠራተኛን የሥራ ውልን መለወጥ ወይም ከስራ ማሰናበት የተከለከለ ነው፡፡ ከሴቶች ሥራ ባለስልጣን ልዩ ፈቃድ ሳይሰጥ፡፡

ከአምስተኛ የእርግዝና ወር ጀምሮ ነፍሰ ጡር ሠራተኛን ለሌሊት ሥራ ማሰራት አይቻልም፡፡

ከወሊድ ዕረፍት የተመለሰችን እሴት ዕረፍት ከመውሰዷ በፊት በነበረችበት ቀድሞ ሥራዋ ለ 60 ቀናት ያህል አሠሪ መመለስ አለበት፡፡